የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድን እና ነዳጅ ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF MINES AND PETROLEUM

ቀን 26 ሰኔ 2012
Date
ቁጥር ሀህ61/9
Ref.No

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
<u>አዲስ አባባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>በሥራ ላይ ያሉ መመሪያዎች እንዲመዘገቡ ስለመጠቅ፡፡</u>

የፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጸድቆ መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረ መመሪያን አዋጁ በወጣ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በመላክ ማስመዝገብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሠረት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን በሥራ ላይ ያሉ መመሪያዎች እንዲመዘገቡ እየጠየቅን የመመሪያዎቹን ቅጂ /ስስ ቅጂን ጨምሮ/ በአጠቃላይ .... ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)
ሚኒስትር

(251-11) 667 55 62
Fax/ፋክስ (251-11)6463364,6463426
486
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

## አባሪ ፩

## በሥራ ላይ ያሉ መመሪያዎች ዝርዝር

1. ከማዕድን ማምረት እና ምርመራ ሥራዎች የሚገኘው የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ሥራ ላይ የሚውልበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2011፤
2. የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ክልሎችን ጣሪያ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/2011፤
3. የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ማመልከቻዎችን ለማስተናገድ የተዘጋጀ የውስጥ አሠራር መመሪያ ቁጥር 4/2011፤
4. የማዕድን ሥራ ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2003፤
5. የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማውጣት መሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2002፤
6. ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ማስገባት ስለሚፈቀድበት ሁኔት የወጣ የማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 4/2001፤
7. የኢታኖል-ቤንዚን ድብልቅ ምርት፣ ሥርጭትና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1/1992፤
8. በማዕድን ሥራዎች ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ፈቃድ ለሚጠይቁ አመልካቾች የወጣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መሥፈርት መመሪያ ቁጥር 3/1990፤
9. የኦፓል ተረፈ ምርት መመሪያ፤ እና
10. የማዕድን ማምረት ሥራ እና የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ የውጭ ሀገር ዜጎች የሚሳተፉበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ መመሪያ::

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum